# ጥናት አንድ ሐዋ ሥራ 17፡1-10(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጳውሎስና ሲላስ በመጀመሪያ ያደረጉት ነገር ወደ ምኩራብ ገብቶ ማስተማር ነው። ሉቃስ ስለ ጳውሎስ የሚናገረው አንድ ነገር ‹‹ጳውሎስም እንደ ልማዱ›› በማለት ጳውሎስ የዘወትር ተግባሩ ወንጌልን ለሌሎች መናገር እንደነበረ እንመለከታለን።
2. የመጀመሪያው ክርስቶስ መከራን መቀበል እንዳለበትና፤ ሁለተኛው ደግሞ ከሙታን መነሳት እንደሚገባው የሚሉት ናቸው። አስረግጠው እንዲያውቁት የፈለገው አንድ ነገር እርሱ የሚሰብክላቸው ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ነው።
3. የእግዚአብሄር ቃል ሲሰራ በቁ5 ላይ እንደምንመለከተው አይሁዶች ቀንተው ወስላቶችንና የመሳሰሉ ሰዎችን በማነሳሳት ወንጌልን ለማዳፈን እንደተነሱ እናያለን። አይሁዶቹ የቀኑበት ምክንያት ሰዎች ሁሉ በኢየሱስ በማመን ህይወታቸው ከተለወጠ ወደ ምኩራባቸው ባዶውን እንደሚቀር፣ የሚሰጣቸው የክብር ስፍራ ሁሉ እንደሚቀር በማሰብና ምናልባትም አንዳንዶች ደግሞ እንደ ጳውሎስ ለእግዚአብሄር የቀኑ እየመሰላቸው ሊኖሩም እንደሚችሉ እገምታሁ።
4. ዕብ 13፡2 እና ሮሜ 12፡13 ለጊዜው ወደ አዕምሮዬ ይመጣሉ። እነርሱን መቀበሉ አደገኛ የሚሆንበት ምክንያት፤ እነዚህ ሰዎች እየታደኑ ያሉና በጥብቅ የሚፈለጉ ሰው ሲሆኑ ራሱን ከነዚህ ሰዎች ጋራ እንኳን ማያያዝ አደገኛ እንደሚሆን አያጠራጥርም።
5. በአማኞቹ ላይ የቀረቡባቸው ክሶች ሁለት ሲሆኑ እነርሱም፤ ኢየሱስ የሚባል ንጉስ አለ ይላሉ፣ የቄሳርን ክስ ይጥሳሉ የሚሉ ናቸው። ኢየሱስ የሚባል ንጉስ አለ ይላሉ የሚለው እውነት ሲሆን እነርሱ በሚሉት ምድራዊ ንጉስነት ግን አይደለም። (ሉቃ 23፡2፣ ዮሐ 19፡12)፤ የቄሳርን ህግ ይጥሳሉ የሚለው ግን መሰረት የሌለው ነው።
6. ህዝቡ የተሸበረበት ምክንያት በነጳውሎስ ላይ የቀረቡት ክሶች ከባዶች ስለሆኑ ይመስለኛል። እነጳውሎስ ደግሞ በአስቸኳይ ወደ ቤርያ በሌሊት የተሸኙት ከዚሁ ከክሱ ክብደት የተነሳና አስከፊ ነገር ሊደርስባቸው እንደሚችል በመረዳት መሆኑን መገመት አያዳግትም።
7. በጳውሎስ ስብከት ያመኑት አይሁዶች፣ እግዚአብሄርን የሚፈሩ ግሪኮች፣ እና እውቅ ሴቶችን ያካትታል። ከዚህ ማየት የምንችለው ንጹህ ወንጌልን ከሰበክን ወንድ ወይም ሴት፣ አይሁድ ወይም ግሪክ፣ ሃብታም ወይም ደሃ ወንጌል ሁሉንም የመለወጥ ሃይል እንዳለው እንማራለን።

# ጥናት ሁለት 1ኛ ተሰ 1፡1-10 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሰላምታ አቅራቢዎች ጳውሎስ፣ ሲላስና ጢሞቲዎስ ሲሆኑ ሰላምታ ተቀባዮቹ ደግሞ የተሰሎንቄ ቤ/ክ ምዕመናን ናቸው። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሄር አብና የኢየሱስ ክርስቶስ ንብረቶች እንደሆኑ ስናይ ይህ ማለትም 1ኛ ቆሮ 6፡19-20 እንደሚናገረው በክርስቶስ ደም የተገዙ ስለሆኑ ከእንግዲህ የራሳቸው ንብረት አለመሆናቸውን ያሳየናል።
2. እነጳውሎስ የሚያደርጉት ነገር ቢኖር በጸሎታቸው ሁሉ ስለእነርሱ እግዚአብሄርን ያመሰግናሉ። የሚያመሰግኑባቸውም ዋነኛ ምክንያቶች፡ ከእምነት ስለሚመነጨው ሥራቸው፣ ከፍቅር ስለሚመነጨው ድካማቸውና ከተስፋ ስለሚመነጨው ጽናታቸው ጌታን ያመሰግናሉ፤
3. ሥራ ሊመነጭ የሚገባው ከእምነት ነው። ይህንን የማደርገው ከፍቅር በመነሳት ነው ወይ የሚለውን ሊጠይቅ ይገባል። እነዚህ ሰዎች በመልካም አጀማመር ላይ እንዳሉ መረዳት የሚቻለው በ1ኛ ቆሮ 13፡13 ላይ ጸንተው እንደሚኖሩ የተነገረላቸው (እምነት፣ ተስፋና ፍቅር) ሶስቱም በህይወታቸው በግልጥ እየሰሩ የሚታዩ በመሆናቸው ነው።
4. ለዚህ ምክንያት አድርጎ ያቀረበው አንድ ምክንያት የወንጌል ወደ ተሰሎንቄ አመጣጥ ነው። ወንጌል ወደነዚህ ሰዎች የመጣው፡ በቃል ብቻ እንዳልሆነ፤ ነገር ግን በሃይል፣ በመንፈስ ቅዱስና በብዙ መረዳት መሆኑን ከቁ5 እንረዳለን።
5. ይህንን ሊያሰኝ የሚችለው፤ አገልጋዮቹ ስለ ተገልጋዮቹ ሲሉ የኖሩት አኗኗርና ተገልጋዮቹ ደግሞ ምሳሌነታቸውን ተከትለው እነርሱን በመምሰል መራመዳቸው ነው። እነርሱ የክርስቶስንና የሃዋርያውን ፈለግ መከተላቸው ለሌሎች ማለትም ለመቄዶንያና ለአካይያ ምዕመናን ምሳሌ ለመሆን እንዳበቃቸው እንመለከታለን።
6. ስለእምነታቸው የሚነገሩት ነገሮች፡ 1) ቃሉን ያመጡላቸውን ሰዎች በምን ዓይነት አቀባበል እንደተቀበሉ፣ 2) ህያውንና እውነተኛውን አምላክ ለማገልገል ከጣዖታት ወደ እግዚአብር እንዴት እንደተመለሱና፣ 3) ከሰማይ የሚመጣውን ኢየሱስን እንዴት እንደሚጠብቁ ነው።
7. ምሳሌው የይሁዳ ቤ/ክ ለተሰሎንቄ ቤ/ክ ነው። (መከራን አቀባበል)፣ ምሳሌዎቹ የተሰሎንቄ አማኞች ሲሆኑ ለመቄዶንያና ለአካይያ አማኞች ነው። (እምነታቸውን አስመልክቶ)፣ በዚህ ክፍል የመቄዶንያ አማኞች ለቆሮንቶስ አማኞች ምሳሌ ሆነው ነው። (ልግስናን አስመልክቶ)
8. እያንዳንዱ አማኝ ወይም ቤተ ክርስትያን ከሌላው ሊማር የሚችለው ብዙ ነገር ስለሚኖር ለአማኝ ትህትናና የተከፈተ ልብ መኖሩ እጅግ የሚያስፈልግ ነገር ነው።

# <u>ጥናት ሶስት 1ኛ ተሰ 2፡1-9 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ምክንያቱም በእነርሱ መምጣት የተነሳ ብዙዎች እንደዳኑና ቤ/ክ እንደተመሰረተች ስለሚያውቁ ነው፡፡ ወንጌል ወደ ተሰሎንቄ የደረሰው በመከራ፣ በመንገላታትና በብዙ ተቃውሞ እንደነበረ ክፍሉ ያሳያል፡፡
2. ከስህተት የመነጨ አይደለም፣ ከክፉ ዓላማ የመነጨ አይደለም፣ ወይም ደግሞ ለማታለል ከመፈለግ የመነጨ አይደለም፤ ወንጌልን ደግሞ እንናገራለን የሚሉት፡ እግዚአብሄር ወንጌልን በአደራ ሲሰጠን ታማኝ አድርጎ እንደቆጠራቸው ሰዎች ሆነን እንናገራለን ይላሉ፡፡
3. ይህንን ያደረጉት ልባቸውን የሚመረምረውን እንጂ ሰዎችን ማስደሰት ዓላማቸው ስላልነበረ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች ሽንገላና፣ አስመሳይነት ናቸው፡፡
4. ምስክር አድርገው የሚጠሩት በቁ5 ላይ ራሳቸውን የተሰሎንቄን ሰዎችና ራሱን የሚያገለግሉትን እግዚአብሄርን ነው፡፡
5. ለአገልግሎታቸው ምላሽ የማይጠብቁት አንድ ነገር ከሰዎች ክብር ለመቀበል አይጠብቁም፡፡ ሃዋርያት እንደመሆናቸው የሚያስፈልጋቸውን እንዲያሟሉላቸው መጠየቅ ሲችሉ እነርሱ ግን አላደረጉትም፡፡
6. ራሱን እንደ እናት አድርጎ ነው የሚያቀርበው፡፡ ይህንን ያለበት ምክንያት ለምዕመናኑ ያለውን እንክብካቤና ልብ ለመጠቆም እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ‹‹ተመላለስን›› የሚለው ቃል አንድ ቀን የመንከባከብ ምልክትን ማሳየት እንዳልሆነና ነገር ግን ጠቅላላ አኗኗራቸው የተመሰረተው በዚያ አይነት እንደነበረ ያስገነዝበናል፡፡
7. ለማካፈል ፈቃደኛ የሆኗቸው ሁለት ነገሮች ወንጌልንና የራሳቸውን ህይወት ነው፡፡ የወንጌሉ ባለቤት እግዚአብሄር እንደሆነ እናያለን፡፡ ባለቤቱ ማን እንደ ሆነ ከልባችን ከተረዳን የምንሰብከው መልዕክት እኛን ወይም ሰዎችን ሳይሆን እርሱን ደስ በማሰኘት ላይ የተመሰረተ ይሆናል ማለት ነው፡፡
8. ወንጌልን ሲሰብኩ ብዙ ጥረት፣ ድካም፣ እንዲሁም ሌሊትና ቀን ሳይቀር በእጃቸው እየሰሩ ወንጌልን መስበክ ነበረ፡፡ በቁ4 መሰረት ይህ ሁሉ ጥረትና ድካም በሙሉ ሰዎች ጎሽ እንዲሏቸው ወይም እንዲያሞግሷቸው ሳይሆን ወንጌልን በአደራ የሰጣቸው እግዚአብሄር ብቻ ደስ እንዲሰኝ በማለት ነው፡፡

# ጥናት አራት 1ኛ ተሰ 2፡10-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በምስክርነት የሚጠሩት የተሰሎንቄ አማኞችንና ራሱን እግዚአብሄርን ነው። ምስክሮቹ ሊመሰክሩ የሚችሉት ነገ፤ እነጳውሎስ በቅድስና፣ በጽድቅና ያለነቀፋ እንደተመላለሱ ነው።
2. የተሰሎንቄ አማኞች ያውቁት የነበረው እውነት እነጳውሎስ ለእነሱ አባት ለልጆቹ እንደሚሆን እንደሆኑላቸው ያውቃሉ። ለጥሪያቸው እንደሚገባ እንዲኖሩ ማበረታታት፣ ማጽናናትና አጥብቆ መለመን ናቸው።
3. ጳውሎስንና ጓደኞቹን ለማያቋርጥ ምስጋና ያነሳሳቸው ነገር፤ የእግዚአብሄርን ቃል እንደ እግዚአብሄር ቃል አድርገው በሙሉ እምነት የመቀበላቸው ጉዳይ ነው።
4. የተሰሎንቄ አማኞች ከይሁዳ አማኞች ጋራ የሚመሳሰሉት፤ ሁለቱም ከየገዛ ወገኖቻቸው መከራን የተቀበሉ መሆናቸው ነው። የእነዚህ ቃላቶች አጠቃቀም ሊያስተምረን የሚችለው ነገር፤ እኛ ሁላችን ከአንድ ቤተሰብ እንደሆንንና እርስ በእርሳችንም ልንተያይ የሚገበን በዚህ መንገድ እንደሆነ ነው።
5. ‹‹እነዚህ›› እያለ የሚናገረው አይሁድን ነው። እነዚህ ሰዎች ያደረጉት፡ ጌታ ኢየሱስንና ነብያትን ገደሉ፣ ሐዋርያትን አሳደዱ፣ እግዚአብሄርን ደስ አላሰኙም፣ የሰው ዘር ሁሉ ፀር ሆኑ። ይህንንም ሁሉ የሚያደርጉት ወንጌል ለአህዛብ እንዳይደርስና ደህንነትን እንዳያገኙ እንደሆነ እንረዳለን።
6. እነዚህን ክርስትያኖች ጳውሎስ ከልቡ እንደሚያፈቅራቸው በግልጽ ማየት እንችላለን። ፊታቸውን ለማየት ብርቱ ጥረት አድርገዋል፣ ወደ እነርሱ ለመምጣት ፈልገዋል፣ በተለይም ጳውሎስ ወደ እነርሱ ለመሄድ ብዙ ጊዜ እንደሞከረ እናነባለን።
7. ጳውሎስ ‹‹ከመጣ›› ሳይሆን ‹‹ሲመጣ›› ማለቱ ስለጌታ ዳግመኛ መምጣት ምንም ዓይነት ጥርጥር እንደሌለው ያስረዳናል። የተሰሎንቄን አማኞች እንደ ተስፋው፣ ደስታውና አክሊሉ አድርጎ እንደሚመለከታቸው እናያለን።
8. ጳውሎስ ትኩረቱ በሚመጣው የጌታ መንግስት ላይ ነው እላለሁ፤ ምክንያቱም ከእነዚህ ሰዎች አሁን ሊገኝ በሚችለው ቁሳቁስ፣ ገንዘብ ወይም ዝና ላይ ሳይሆን ትኩረቱ በእርሱ አነጋገር ‹‹ጌታ ሲመጣ›› በእነርሱ ምክንያት ስለሚያገኛቸው በረከቶች ነው አስረግጦ የተናገረው።

# ጥናት አምስት 1ኛ ተሰ 3፡1-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ክፍል መታገስ አልቻልንም የሚለው ከላይ በምዕራፍ ሁለት መጨረሻ ላይ የተናገረውን ናፍቆታቸውን ነው መታገስ ያልቻሉት፡፡ ጢሞቲዎስ የተላከበት ምክንያት በእምነታቸው እንዲያጸናቸውና እንዲያበረታታቸው ነው፡፡ እነጳውሎስ መስዋዕት ከፍለዋል ማለት የምንችለውን፤ በቁ1 እንደምናየው ብቻቸውን ለመቅረትና በአገልግሎታቸው የሚረዳቸውን ነው የላኩት፡፡
2. የጢሞቲዎስ ለማጽናናትና ለማበረታታት መላክ በተለይ እነዚህ ሰዎች በጊዜው በፈተና ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው ተልዕኮውን ወቅታዊ ያደርገዋል፡፡ ‹‹እኛም ለዚህ ነገር እንደተመደብን…›› የሚለው አነጋገሩን የምረዳው በ2ኛ ጢሞ 3፡12 ላይ እንደሚናገረው ጌታን እየመሰልን ለመኖር የቆረጥን ሰዎች ክርስትናን መከራን ለይተን ማየት እንደማንችል ሲገልጽ ይመስለኛል፡፡
3. የጳውሎስ ፍርሃት ምናልባት ፈታኙ ሰይጣን ፈትኖአቸው ተሸንፈው ይሆናል የሚል ነበረ፡፡ ጢሞቲዎስ እምነታቸውን ከማጽናት ሌላ አስቀድሞ እነዚህ አማኞች እምነታቸው በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ማረጋገጥና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ነው፡፡
4. የፈሩት ፍቅራቸውም ሆነ እምነታቸውም እነሱ ካሰቡት በተሻለ ሁኔታ እንደሚገኝ አረጋገጠላቸው፡፡ ፍርሃታቸው መሰረት አልነበረውም፤ ምክንያቱም እግዚአብሄር ራሱ ከልጆቹ ጋራ እንደሚሆንና በመከራም ውስጥ ሁሉ ሊያቆማቸው የሚችል እርሱ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡
5. ለእነጳውሎስ መጽናናት የሆናቸው ነገር የተሰሎንቄ ሰዎች በእምነታቸው ጸንተው መቆማቸው ነው፡፡ በነጳውሎስ ውስጥ የፈጠረው ሌላ ስሜት የማይነገር አይነት ደስታ ሲሆን፤ ለዚህም ምክንያቱ እንደሚመስለኝ በብዙ ስደትና መከታ ወንጌልን ያደረሱላቸው ሰዎች ስለሆኑ የእነርሱ መውደቅ የድካማቸው ፍሬ ከንቱ እንደመሚሆን ስለቆጠሩት ይመስለኛል፡፡
6. እነዚህን ወገኖች ለማግኘት ከልባቸው እንደፈለጉ የምናውቀው በቁ10 ላይ የጸሎቱና አይነት ስናይ እንዲሁ ትዝ ባላቸው ቀን ሳይሆን ‹‹ሌሊትና ቀን እጅግ ተግተን እንጸልያለን›› ነው የሚለው፡፡ ይህ የሚያሳየን ቆራጥ የሆነ ውሳኔ እንዳደረጉ ነው፡፡ ይህ አነጋገር በጸሎታቸው ሁሉ ውስጥና በቀኑም ውሎአቸው ባይንበረከኩም እግዚአብሄርን የማሳሰብን ሁኔታ እንጂ ሲጸልዩ ውሎ ሲጸልዩ ማደርን የሚያሳይ አይመስለኝም፡፡
7. የመጀመሪያው የእርስ በእርስ ፍቅራቸውን እንዲያበዛና እንዲያትረፈርፍላቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ጌታ ሲመጣ ነቀፋ የለለባቸውና ቅዱሳን ሆነው እንዲገኙ ነው፡፡
8. በተደጋጋሚ የነገሯቸው ነገር አማኞች መከራ እንደሚያገኛቸው ነው፡፡ ይህ ትምህርት ከዛሬው ዘመን ትምህርት ጋራ የማይጣጣምና አብሮ የማይሄድ ነው፡፡ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች የእግዚአብሄርን ፈቃድ ሁሉ፤ ማለትም አማኞች ከሆኑ መከራ እንደሚደርስባቸውም ጭምር አስተምሯቸዋል ማለት ነው፡፡

## <u>ጥናት ስድስት 1ኛ ተሰ 4፡1-10 ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. እነዚህ አማኞች የተማሩት ነገር እግዚአብሄርን ደስ ለማሰኘት እንዴት መኖር እንደሚገባ ነው፡፡ ኑሯቸውና ትምህርቱ የተጣጣመ እንደነበረ እዚሁ ክፍል ላይ እናነባለን፡፡
2. የሚለምኗቸው በፊት ካደረጉት በላይ እግዚአብሄርን ደስ በማሰኘት እንዲመላለሱ ነው፡፡ ሥልጣን የሚለውን ሃሳብ የተጠቀመበት ምክንያት እንደሚመስለኝ የእግዚአብሄርን ቃል ወይም ትእዛዝ የሚናገር ማንኛውም ሰው በስልጣን መናገር ይችላል፤ ምክንያቱም ስልጣኑ ከቃሉ እንጂ ከሰውየው ስላልሆነ ነው፡፡ ማድረግና አለማድረግ ግን የሰዎቹ ፈንታ ስለሆነ ማበረታታትና በፍቅር መናገር የበለጠ ልባቸውን ለመክፈት ይረዳል እላለሁ፡፡
3. ሶስቱ ነገሮች ከዝሙት መራቅ፣ መቀደስና፣ እያንዳንዱ የገዛ ሰውነቱን በቅድስናና በክብር መያዝ እንዳለበት እንዲያውቅ ነው፡፡ ምክንያቱም በቃሉ ግልጽ ሆኖ ስለተነገረና የእግዚአብሄር ፈቃድ ምን እንደሆነ በግልጽ ስለተነገረን እነዚህ ነገሮች ጸሎት አያስፈልጋቸውም፡፡
4. ሁለቱ ነገሮች እንደነገሯቸውና እንዳስጠነቀቋቸው ነው የሚናገረው፡፡ እነዚህ የአህዛብና እግዚአብሄርን የማያውቁ ሰዎች ተግባር ሆነው ነው የተነገሩት፡፡ እግዚአብሄር እንደማይቀልድ የሚያሳየን ቁ6 ላይ የሚናገረው ‹‹ጌታ እንደዚህ ያለውን ሃጥያት ሁሉ የሚፈጽሙትን ይበቀላል›› ይላል፡፡
5. የተጠራነው በቅድስና እንድንመላለስ ሲሆን ለርኩሰት ግን አልተጠራንም፡፡ ለቅድስና የተጠራንበት ምክንያት ብዬ የማምነው አባታችን ወይም የጠራን እርሱ ቅዱስ ስለሆነ የልጁን መልክ እንድንመስል ስለተጠራንና አድራሻችን ያ ስለሆነ ነው፡፡ ይህ ትዝ የሚያሰኘኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል 1ኛ ጴጥ 1፡16 ‹‹እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ›› የሚለው ነው፡፡
6. ቃሉን ለመታዘዝ እንቢተኛነትን ለምናሳይ ሰዎች መልዕክቱ፡ የናቅነው የነገረንን ሰው ሳይሆን በእርሱ ውስጥ ቃሉን ያስተላለፈውን እግዚአብሄርን እንደሆነ ነው፡፡ ቃሉን ነግረናቸው አልሰማና አልታዘዝ ቢሉ ቁ6 እንደሚናገር የሚበቀለው እርሱ ስለሆነ ከመጸለይ ሌላ ማድረግ የምንችለው ነገር የለም፡፡
7. በመሃላቸው የምናየው አንዱ በረከት የእርስ በእርስ ወይም የወንድማማች መዋደድ ነው፡፡ ይህ ነገር በዘመናት ሁሉ አስፈላጊ ሆኖ የሚገኘው፤ በመጀመሪያ ደረጃ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት መሆናችንን አለም የሚያይበት ነገር ሲሆን ሌላው ደግሞ ወንጌልን በህብረት ለመስራት ፍቅር ከሌለ የማይቻል ተራራን እንደመግፋት ስለሆነ ነው፡፡
8. በዚህ ክፍል ምክሩ በፍቅራቸው ከበፊቱ ይልቅ አብልጠው እንዲገፉበት ነው፡፡ ይህንን ያለበት ምክንያት ማናቸውም የመንፈስ ፍሬዎች በህይወታችን ቢኖሩም እለት እለት ሊያድጉና ሊጨምሩ እንደሚገባቸው ሲያስገነዝባቸው ነው፡፡ በህይወትህ ያሉትን የመንፈስ ፍሬዎች ሁሉ በቃ ደረስኩ ሳትል ልትኮተኩትና ልታሳድጋቸው እንደሚገባህ አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ሰባት 1ኛ ተሰ 4፡11-18 ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ትዕዛዞቹ በገዛ እጅ እንዲሰሩ፣ በጸጥታ እንዲኖሩና በራሳቸው ጉዳይ ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ የሚሉት ናቸው፡፡ ስንት ጊዜ እንዳዘዟቸው ባይታወቅም ከሁለት ጊዜ በላይ እንደሆነ ይጠቁመናል፡፡ እነዚህን አነጋገሮች ሳይ እነጳውሎስ ነገሮችን አንድ ጊዜ ብቻ በመንገር በቃ ብለው እንደማይተውና በመደጋገም ማስታወስ አስፈላጊ እንደሆነ የሚያምኑ ይመስላል፡፡
2. አንደኛው በውጭ ባሉት ዘንድ እንዲያስከብራቸው፣ ሌላው ደግሞ በማንም ሰው ላይ ሸክም እንዳይሆኑ የሚሉት ናቸው፡፡ በውጭ ያሉት ሰዎች ወንጌል ሲነገራቸው የምንነግራቸውን ቃላት ብቻ ሳይሆን የምንኖረውን የህይወት አይነት በደንብ ስለሚመለከቱ ለወንጌል እንቅፋት እንዳንሆን ነው፡፡
3. አብዛኛውን ጊዜ በራሴም ሆነ በቤተክርስትያን ጎልቶ የማየው ችግር በሰዎች ነገር ጣልቃ መግባት ነው፡፡ በራስ ጉዳይ ላይ ብቻ አለማተኮር የሚያስከትሉት ነገሮች፤ የሌሎችን ነገር ስናወጣና ስናወርድ የራሳችን የሆኑትን ነገሮች ለማከናወን ጊዜ ያሳጥርብናል፣ የማያስፈልግ ሃጥያት ውስጥ ይከተናል፣ ራሳችንን ከሌሎች ጋራ የማወዳደር ህይወትም ውስጥ ሊያስገባን ይችላል፡፡
4. እንዲያውቁ የሚፈልገው ነገር አንቀላፍተው ወይም ሞተው ስላሉት ሰዎች ሁኔታ ነው፡፡ እያነጻጸረ የሚናገረው ከሌሎች ሰዎች ማለትም ከአህዛብ ጋራ ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ አማኞች አይዘኑ ማለት ሳይሆን የአህዛብ አይነት ራስን በመጉዳትና ያንቀላፋው ሰው ወደፊት ተስፋ እንደሌለው አድርጎ ሃዘንን ማብዛት ለሚመለከት ሰው ትክክለኛ መልዕክት አያስተላልፍም ማለት ነው፡፡
5. አማኞች ከሙታን መነሳታቸውን ከማመናችን አስቀድሞ ማመን የሚኖርብን እውነት፤ የክርስቶስን መሞትና ከሙታን ደግሞ መነሳት ነው፡፡ ጳውሎስ ምክንያት አድርጎ የሚናገረው ክርስቶስ አልተነሳም ከተባለ እኛም ከሙታን መነሳታችን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ እምነታችን በክርስቶስ መነሳት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ይነግረናል፡፡
6. ‹‹አስቀድመው ይነሳሉ›› ሲል እኛ ወደ ክርስቶስ ለብቻችን የምንነጠቅ ሳይሆን እነርሱን እንደምንጠብቅ ለማሳየት ነው፡፡ ለዚህም ቁ15 ላይ ‹‹እኛ በህይወት ያለንና ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉትን አንቀድምም›› የሚለው ሃሳብና፤ በቁ17 ላይ ደግሞ ‹‹ከእነርሱ ጋራ በደመና እንነጠቃለን›› የሚሉት አነጋገሮች ይህንን ሃሳብ ይደግፋሉ፡፡
7. በታላቅ ትዕዛዝ፣ በመላዕክት አለቃ ድምጽና፣ በእግዚአብሄር መለከት ድምጽ የሚሉት ናቸው፡፡ የማያቸው አራት ነገሮች 1) ቁ16 ላይ ያለው የጌታ ከሰማይ መውረድ 2) ቁ16 በክርስቶስ የሞቱት መነሳት 3) በህይወት የሚቀሩትና የተነሱት ሙታን በአንድነት በደመና መነጠቅ 4) ለዘለዓለም ከጌታ ጋራ መሆን የሚሉት ናቸው፡፡
8. ጳውሎስ እነዚህን እውነቶች ሁሉ መናገሩ በቁ18 ላይ እንደተናገረው ቅዱሳኑ እርስ በእርሳቸው በዚህ እውነት እንዲበረታቱና እንዲጽናኑ እንደሆነ መረዳት እንችላለን፡፡

# ጥናት ስምንት 1ኛ ተሰ 5፡1-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ስለ ዘመናትና ስለወራት መጻፍ ያላስፈለገው እነርሱ ስለዚህ ጉዳይ በቂ የሆነ እውቀት ስላላቸው እንደሆነ ይነግረናል። 1ኛ ተሰ 3፡4 4፡6 እና 4፡11 የመሳሰሉትን ስናነብ እነጳውሎስ ነገሮችን ቀደም ብለው እንዳስተማሯቸው ስለምናይ ይህንንም እውነት ከእነርሱ ከራሳቸው እንደተማሩት ነው የማምነው።
2. የመጀመሪያው ከሌባ ጋራ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከምጥ ጋራ ነው። እነዚህን ነገሮች ከጌታ ምጽአት ጋራ የሚያመሳስላቸው ዋነኛ ነገር ድንገተኛነታቸውና ትክክለኛው ጊዜ ያለመታወቁ ሁኔታ ነው።
3. ‹‹ሰዎች›› የሚላቸው በክርስቶስ ያላመኑትን ሰዎች ነው፤ ምክንያቱም በዚሁ ቁጥር ላይ ሲናገር ‹‹ይመጣባቸዋል‹‹ ‹‹አያመልጡም›› በማለት በሶስተኛ ሰው ይናገራል። በተጨማሪም ቁ4ትን ስናነብ አማኞችን ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ያደርግልናል።
4. ‹‹እናንተ ግን›› በማለት የሚናገረው ስለአማኞች ማለትም ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ለወጡት በሙሉ ነው። አማኝ የጌታን መገለጥ መፍራት ስለማይኖርበት ምክንያት በቁ4-5 ላይ በተለያየ መንገድ በመጠቀም አንዱን እውነት በተለያየ መንገድ ገልጾታል፡ በጨለማ ውስጥ ስላልሆነ፣ የብርሃን ልጅ ስለሆነ፣ የቀን ልጅ ስለሆነ፣ ከሌሊት ወይም ከጨለማ ወገን ስላይደለ ነው።
5. የመጀመሪያው እንዲነቁ ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ ራሳቸውን እንዲገዙ ነው። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ አማኞችን ከሚያንቀላፉትና ከሚሰክሩት ሰዎች ጋራ ሲሆን፤ ምክንያቱም የሚያንቀላፉም ሆኑ የሚሰክሩ ሰዎች በአብዛኛው የሚተኙትና የሚሰክሩት በሌሊት ወይም በጨለማ ስለሆነ አማኝ ደግሞ በጨለማና በሌሊት ውስጥ ስላልሆነ እንቅልፍም ሆነ ስካር ሳይሆን በመንቃትና ራስን በመግዛር ሊኖር ይጠበቅበታል።
6. የቀን ሰዎች የሆኑ ሁሉ እምነትንና ፍቅርን እንደ ጥሩር መልበስ፤ የመዳንን ተስፋ እንደ ራስ ቁር መድፋት፤ እና ራሳቸውን በመግዛት መኖር ይጠበቅባቸዋል።
7. እነዚህ ሁለት እንቅልፎች አንድ አይነት ናቸው ብዬ አላምንም፤ ምክንያቱም በቀ7 ላይ የሚናገረው እንቅልፍ ያላመኑ ሰዎች የሚኖሩትን የህይወት አይነት ለማሳየት የተጠቀመበት ሲሆን፤ በቁ10 ላይ የምናየው ግን ጳውሎስ ራሱንም ጨምሮ ስለአማኞች ሞት ለመናገር የተጠቀመበት አነጋገር ነው። በዚህ ቁጥር አነጋገር ክርስቶስ ስለእኛ የሞተበት ምክንያት ‹‹ብንነቃም ሆነ ብናንቀላፋ ከእርሱ ጋራ በህይወት እንድንኖር›› ነው በማለት ይነግረናል።
8. አማኞችን በዚህ ቁጥር ላይ የሚያበረታታው እርስ በእርሳቸው እንዲጽናናኑና፤ አንዱ ሌላውን እንዲያንጸው ነው። የተሰሎንቄ አማኞች እነዚህን ሁለት ነገሮች በህይወታቸው እርስ በእርስ እየተለማመዱት እንዳሉ የምናነብ ሲሆን፤ እነዚህን ሰዎች ሃዋርያው የሚያበረታታው በያዙት ነገር እንዲገፉበትና እንዳያቋርጡ ነው የሚነግራቸው።

# ጥናት ዘጠኝ 1ኛ ተሰ 5፡12-28 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እንድናከብር የሚለምነን በትጋት የሚሰሩትን፣ በጌታ የበላዮቻችን የሆኑትንና፤ እንዲሁም በጌታ መካሪዎቻችን የሆኑትን ነው፡፡ ‹‹የበላዮቻችሁ›› የሚለው አነጋገር ከ1ኛ ጴጥ 5፡3 ጋራ ስመለከተው ስለ ቤተክርስትያን ሽማግሌዎች ነው ብዬ አምናለሁ፡፡
2. እነዚህ ሰዎች ፍቅር የተሞላበት እጅግ የሆነ አክብሮት እንዲሰጣቸው ስላዘዘበት ምክንያት ቁ13 በአጭሩ ‹‹ስለ ሥራቸው›› በማለት ይነግረናል፡፡
3. ሥራ ፈቶች፣ ፈሪዎችና ደካሞች ሲሆን፤ ለነዚህም ሰዎች አማኝ እንዲወስድ የተነገረው እርምጃ፤ ለስራ ፈት ተግሳጽ፣ ለፈሪ ማደፋፈርና፣ ለደካማ ደግሞ እርዳታ እንደሆነ ከምክሩ እናያለን፡፡ ለእያንዳንዱ የራሱ የሆነ መፍትሄን መናገሩ ሁሉም አይነት ችግር በአንድ አይነት መንገድ ሊፈታ እንደማይችልና እንደ ችግሩ መፍትሔውም ሌላ ሊሆን እንደሚገባ እንማራለን፡፡
4. አጥብቆ የሚያስጠነቅቀው ነገር በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልሱ ነው፡፡ የሚያበረታታቸው ደግሞ ለሰዎች ሁልጊዜ መልካም የሆነውን ነገር ለማድረግ እንዲጥሩ ነው፡፡ ‹‹ተጣጣሩ›› ሲል በቀላሉ የሚመጣ ነገር እንዳልሆነና ጸሎትን፣ ሲሸነፉ እንደገና መመከርን፣ ተስፋ አለመቁረጥን ሁሉ የሚያካትት እንደሆነ እመለከታለሁ፡፡
5. በነዚህ ሶስት ቁጥሮች ውስጥ የተጠቀሱት ሶስት ነገሮች ማለትም ሁልጊዜ ደስ መሰኘት፣ ሳያቋርጡ መጸለይና፣ በማናቸውም ሁኔታ እግዚአብሄርን ማመስገን የእግዚአብሄር ፈቃድ እንደሆነ እናያለን፡፡ ይህም ማለት ደስታን በተመለከተ ሁኔታዎች ለደስታችን ምንጭ ሳይሆኑ ጌታ እንዲሆን ፊሊ 4፡4፤ ጸሎት ደግሞ በተንበረከክን ሰዓት ብቻ ሳይሆን ያልተቋረጠ ግንኙነት እንዲኖረን፣ ምስጋና ደግሞ ክፉም ሆነ መልካም በሚመስሉን ሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ ምስጋንን መስጠት ማለት ነው፡፡
6. አምስቱም ምዕራፎች በየመዝጊያቸው ላይ እየጠቀሱ ያለፉትና ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸው ርዕስ የጌታ ምጽአት ጉዳይ ነው፡፡ ለጌታ ምጽአት መንፈሳችን፣ ነፍሳችንና፣ ሥጋችን ያለነቀፋ እንዲጠበቁ የተነገረን ሲሆን፣ በዚያው ቁጥር ላይ እንደሚነግረን ይህ በሰው ሃይል ሊሰራ የሚችል እንዳልሆነና ታማኝ የሆነው እግዚአብሄር ራሱ በህይወታችን እንደሚያከናውነው ይነግረናል፡፡
7. የመንፈስን እሳት እንዳናዳፍን፣ ትንቢትን እንዳንንቅ፣ ሁሉን ነገር እንድንፈትን፣ መልካም የሆነውን እንድንይዝና፣ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር እንድንርቅ ነው፡፡ ሰዎቹ የተጠቀሙበት መመሪያ ሁሉን ነገር ፈትኑ የሚለውን ሲሆን፤ ለመፈተን የተጠቀሙበትም የእግዚአብሄርን ቃል እንደሆነ እናያለን፡፡